የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር፮ አይሳኢታ -ሐምሌ ፰ ቀን ፲፱፱፯ዓ.ም	በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ምክር-ቤት ጠባቂነት የወጣ	2nd Year No.6 AYSAITA-8th JULY.1999

አ
አ
አ

T¨<Ý

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን (ሴክተር ቢሮዎችን) ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ.....ገጽ፩

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን (ሴክተር ቢሮዎችን)ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፮/፲፱፱፯ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲምክራሲያዊ ሪፐብሊስ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ ፶፪ በንዑስ ቁጥር፪/ለ/ እና በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ ፶፯ ንኡስ ቁጥር ፪፪ መሰረት የሚከተሉት የሴክተር ቢሮዎች (አስፈጻሚ አካላት) ተቋቁመዋል።

፩.የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣

፪.የፋይናንስ ቢሮ

፫.የግብርና ቢሮ፣

፬.የከተማ ልማት፣ማእድንና ኢነርጂ ቢሮ፣

፭.የትምህርትና ባህል ቢሮ፣

፮.የጤና ቢሮ፣

፯.የንግድ፣ኢንዱስትሪ ትራንስፖርትና ተሪዝም ቢሮ፣

፰.የአደጋ መከላከልና የሰራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣

፱.የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ

፲.የኦዲት ቢሮ

፲፩.የውሃ ሀብት ልማት ቢሮ

፲፪.የፍትህ ቢሮ

፲፫. የአካል ማስልጠኛና ስፖርት ኮሚሽን የቢሮዎች የወል ሥልጣንና ተግባር፣

እያንዳንዱ ቢሮ

Ñ ጽ ፪ የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር ፯ ሐምሌ ፭ ቀን ፲፱፻፯፭ ዓ.ም

፭.በሥራው መስክ

ሀ) እቅድና በጀት ያዘጋጃል በሥራ ላይ ያውላል።

ለ) ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ያወጣል በስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

ሐ) የጥናትና ምርምር ተግባር ያከናውናል፣ የስታትስቲክስ መረጃዎች ይሰበስባል ያቀነባብራል፣ ለሚመለከተው የማዕከላዊ መንግሥትና የክልል አስፈጻሚ አካላት ያስተላልፋል፣

መ) በሕግ መሰረት ውሎችን ይዋዋላል።

፪.በዚህ አዋጅ የተመለከቱትንና በሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል።

፫.ስለሥራው ክንዋኔ በየወቅቱ ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ለሚመለከተው የማዕከላዊ መንግሥት አስፈጻሚ አካል ዘገባ ያቀርባል።

፬. በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባር ለማስፈጸም በየደረጃው እንደአስፈላጊነቱ ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ፣፩.

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር።

የክልሉ የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

፩.የሀገሪቱን የልማት ስትራቴጂና በአጠቃላይ ፖሊሲን መሰረት በማድረግ በክልሉ መንግስት የሚፈጸም የረጅም የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የልማት እቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል።

፪.የአፋር ሕዝብ ካለበት የተበታተነ የዘላንነት ኑሮ እንዲላቀቅ ዘለቄታ ያለውና የተረጋጋ ቋሚ ኑሮ ለመመሥረት እንዲቻል ልዩ ትኩረት በመስጠት በቀጣይነት ያቅዳል፣ ያስተባብራል፣ያስፈጽማል፣ይቆጣጠራል።

፫. ከሚመለከታቸው የክልል መንግሥት አካላት ጋር በመተባበር በረጅም፣ በመካከለኛና በአጭር ጊዜ እቅድ ውስጥ የሚንፀባረቁ በክልሉ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች እንዲጠኑና እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ይገመግማል።

፬. በክልል መንግሥት አካላት እየተዘጋጁ የሚቀርቡለትን ዓመታዊ የልማት እቅዶችና ለነዚሁም የሚያስፈልጉ የካፒታል በጀት ጥያቄዎችን መርምሮ የተጠቃለለ የልማት እቅድና የካፒታል በጀት አዘጋጅቶ ከክልል መንግሥቱ ዓመታዊ ጠቅላላ በጀት ጋር ተዋህዶ እንዲቀርብ ለክልሉ የፋይናንስ ቢሮ ያስተላልፋል።ሲፈቀድም አፈጻጸሙን ይከታተላል።

፭. ከአገሪቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አንጻር በክልሉ የግል ክፍለ ኢኮኖሚ ተሣትፎ እንዲበረታታ ድጋፍ ሰጪ የሆኑ አመልካች እቅድ ያዘጋጃል፣

፮. የክልሉ የረዥም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የልማት እቅድ ለማዘጋጀት የሚረዳ የክልሉ የምርት ስፔሻላይዜ ሽንና የተለየ የማልማት አቅም ሁኔታዎች በሚመለከት ኢኮኖሚ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል።

፯. ከኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር የሚተላለፉትን የፕላን አዘገጃጀት እና አቀራረብ መመሪያዎች ለክልሉ አሠራር አመቺ በሆነ መልክ ያብራራል፣ ለክልሉ መስተዳድር አካላት በወቅቱ እንዲደርስ ያደርጋል።

፰.የክልሉ የተፈጥሮ ሀብት፣የሕዝብ፣የሣይንስና የቴክኖሎጂ ሥርጭትን አገልግሎት መረጃዎችን ይሰበስባል. ለክልሉ ልማትና እቅድ የሚያስፈልጉ የቅየሳ፣ የካርታና የጂኦግራፊ ጥናት ሥራዎች እንዲከናወኑ ያደርጋል

Ñ ጽ ፪ የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር ፯ ሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም

፲. ስለሥራው ክንዋኔ ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ለኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ወቅታዊ ዘገባ ያቀርባል፣

አንቀጽ፪

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ ቢሮ

ሥልጣንና ተግብር

፩. የክልሉ መስተዳድር አካላት የመንግሥት ፋይናንስ ፖሊሲዎችን፤ሕጎችን ፣ደንቦችንና መመሪያዎችን ተከትለው መሥራታቸውን ይቆጣጠራል፣

፪. ከክልሉ የተለያዩ የመስተዳድር አካላት እየተዘጋጁ የሚቀርቡትን መደበኛ በጀትና ከፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ተዘጋጅተው የሚቀርቡለትን የካፒታል በጀት እየመረመረ ዓመታዊ በጀት አጠቃሎ በማዘጋጀት ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኪሚቴ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ያስተዳድራል፣

፫. ከማናቸውም የገቢ ምንጭ የሚገኘውን ግብር በሕጉ መሰረት መወሰኑን፣በወቅቱ ተሰብስቦ ገቢ መደረጉንና ሂሳቡም በአግባቡ፣ መያዙን ያረጋግጣል፣

፬. የክልሉ መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓትን ይመሰርታል፣ መመሪያ ያወጣል፣ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፣

፭. የክልል መንግሥት ከሀገር ውስጥ ባንኮች የሚገኘውን ብድር በመንግሥት ስም ተደራድሮ ጥፈርማል፣ብድሮቹን እየተቆጣጠረ ያስተዳድራል፣

፮. የክልሉ መንግሥት አክሲዮኖች የሚተላለፉና የማይተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችንና ሌሎች ተመሣሣይ ተቀማጭ የገንዘብ ሀብቶችን ይይዛል፣ይጠብቃል

፯. የክልሉ መ/ቤቶች የዕቃ ገዥ ንብረት አጠባበቅና አጠቃቀም መመሪያ ያወጣል፣ተግባራዊነቱንም ይቆጣጠራል፣

፰. በሌላ የክልሉ መንግሥት አካላት የማይተዳደር፣ወይም ጥቅም ላይ ያልዋለ የመስተዳድሩ የመንግሥት ንብረት ኃላፊ ሆኖ ያስተዳድራል።

፱. ስለክልሉ የፋይናንስ አሰባሰብ፣አያያዝ፣አጠቃቀም ጥናት እያደረገ የመፍትሄ ሀሳብ ያመነጫል፣ም/ቤቱን ያማክራል፣

፲. ክልል መንግሥቱ የፋይናንስ ክንውን፣የገንዘብ ይዞታና አስተዳደር የማያስረዳ ጠቅላላ መግለጫ በየወቅቱ ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣ለዓመቱ ከተዘጋጀው በጀት ላይ ተጨማሪ በጀት ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና በተገቢ አካል ሲፈቀድ አዘጋጅቶ ያቀርባል።

አንቀጽ ፭

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የግብርና ቢሮ ሥልጣንና ተግባር፣

የክልሉ የግብርና ቢሮ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡

፩. የሀገሪቱን የግብርና ልማት ፖሊሲ መሰረት በማድረግ በክልሉ የግብርና ልማት እንዲስፋፋ ያበረታታል፣የመሬት አጠቃቀምና ድልድል በሀገሪቱ የመሬት አጠቃቀም ፖሊስ መሰረት መፈጸሙን ያረጋግጣል፡

፪. ለክልሉ እንስሳት አርቢዎች የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ይሰጣል፡

፫. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ምርጥ የእንስሳት ዘር አቅርቦት የግብርና ምርት ማሣደጊያዎች፣የእርሻ መሣሪያዎችን በብድር አገልግሎት እንዲቀርቡ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፡

፬. የክልሉን የግብርና ልማት ለማፈጠን የሚረዳ የምርምርና የሥልጠና ፕሮግራምችን ያካሂዳል፣አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የገጠር ጤክኖሎጂ እንዲዳብር ያደርጋል፣ል፣ያጠናቅራል፣ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል፡

Ñ ጽ ፪ የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር ፯ ሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም

፭. ለምርጥ የእንስሳትና የአሣ ዝርያዎችንና ለተሻሻሉ ዘሮችነ ማባዣ የሚያስፈልጉ ዘር ማባዣ ማእከላትን ያደራጃል፡

፮. ዘመናዊ የእንስሳት እርባታና የእርሻ ሥራ ማህበራትን እንዲስፋፋ ያደርጋል ይመዘግባል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡

፯. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የግብርና ኤንቨስትመንት እንዲበረታታ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ለአገር ውስጥ ኢንቨስተሮች የግብርና ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል

፲. የሀገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አካባቢ ጥበቃ ፖሊሲዎች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል

፱. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የሽለቆዎች፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን ክምችትና ሥርጭት በማጥናት መረጃዎችን በመሠብሰብና በመመዝገብ ረገድ ይተባበራል።

፲. ስለደንና ስለዱር አራዊት ሀብት ልማትና ጥበቃ አጠቃቀም የወጡ ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል።

፲፩. የክልሉን የደንና የዱር አራዋት ሀብት እንዲጠበቅና እንዲለማ ያደርጋል፣ አጠቃቀሙን በሕጋዊ መንገድ መፈጸሙን ይቆጣጠራል፣

፲፪. የክልሉን ውስጥ የሚገኙ ለአደን የተከለከሉ ቦታዎችንና ጥበቅ ደኖችን ያስተዳድራል፣

፲፫. የክሉ የደን ልማት እንዲስፋፋ ያበረታታል፣ በቂ የሆነ የደን ዛፍ ችግኞችና የቴክኒክ አገልግሎት እንዲዳረስ ጥረት ያደርጋል፣

፲፬. የሜትሮሎጂ መረጃዎችን በመሰብሰብ ረገድ አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል፣

፲፭. በክልሉ የገጠር ልማትና ለማፋጠን የሚያስችሉ የእንስሳት ጤና ክሊኒኮች፣ ላቦራቶሮች፣ የገጠር ቴክኖሎጂ ማዕከላትን፣ የችግኝ ጣቢያዎችንና ሌሎች ተቋማትን ያደራጃል፣ ያቋቁማል፣

፲፮. በክልሉ የእንስሳትና የሰብል ዝርያዎች እንቅስቃሴ ቁጥጥር ያደርጋል፣በሕገ ወጥ እንቅስቃሴዎች ላይ እርምጃ ይወስዳል፣

፲፯. ወደ ክልል በሚገቡትም ሆነ በሚወጡ በክልሉ ውስጥ ጭምር የዕፅዋት፣የአዝርዕት እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ላይ ተገቢውን የኳራንቴን ቁጥጥር ያደርጋል፣

፲፰. የአፋር ሕዝብ ከተበታተነ የዘላንነት ኑሮ ተላቆ ዘላቂ ኒሮ ለመመሥራት የሚያስችለውን ዘመናዊ የእንስሳት እርባታና የእርሻ ሥራ እንዲለመድ እና እንዲያስፋፋ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።

አንቀጽ ፬

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሥራና ከተማ ልማት፣የማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

የክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፣

፩. የኮንስትራክሽን፣ የከተማ ልማትና ቤት ፖሊሲዎችን በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

፪. የሕንፃ ኮድ፣የዲዛይንና የኮንስትራክሽን ሥራ ደረጃዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፣

፫. በክልሉ በጀት የሚሰሩ የመንግሥት ኮንስትራክሽኖች እንዲሰሩ፣ እንዲሻሻሉና እንዲጠገኑ ያደርጋል፣

፬. በክልሉ በጀት ለሚሠሩ የመንግሥት ኮንስትራክሽኖች የሚያስፈልጉ ዲዛይኖችና የኮንስትራክሽን ሥራዎችን ውሎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣

፭. በክልሉ በጀት የሚከናወኑ የመንግሥት ኮንስትራክሽን በተገባለት ውል መሰረት የጥናት ደረጃ የጊዜውና የዋጋ ገደቦች ተጠብቀው መሰራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቁጥጥር እንዲኖር ያደርጋል፣ በበላይነት፣ይቆጣጠራል

Ñ ጽ ፪ የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር ፯ ሐምሌ ፭ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

፮. በክልሉ ደረጃ ተወዳድሮ መሰራት የሚችሉ የሀገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣

፯. ለከተሞች መሪ ፕላን ዝግጅት የሚረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ የከተሞች መሪ ፕላኖች ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ዝርዝር ፕላኖች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ አፈጻጸመቻውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፰. በክልሉ ባለቤትነት ሥራ የሚገኙ የከተማ ልማት ቤቶችን ያስተዳድራል፣እንዲታደሱና እንዲጠገኑ ያደርጋል፣

፱. በክልል ከተሞች ውስጥ የመኖሪያ ቤትን ችግር ለማቃለል የቁጠባ ቤቶችን እንዲሠሩና እንዲከራዩ ወይም እንዲሸጡ ያደርጋል፣

፲. የጎብረት ሥራ ማህበራትን ይመዘግባል፣ ያበረታታል ድጋፍ ይሰጣል፣

፲፩. በክልሉ የሚገኙትን ቻርተር ያልተሰጣቸው ማዘጋጃ ቤቶችን በበጀት በዕቅድና በከተማ ፕላን አዘጋጃጀትና አፈጻጸም በሰው ኃይል ሥምሪት በአስተዳደርና ገቢ አሰባሰብ ረገድ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣የቴክኒክ፣የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፣

፲፪. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለክልሉ የሚያስፈልጉ ጋዝ፣ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች የሚቀርቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

፲፫. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለክልሉ የተወሰነ ኢነርጂ መጠባበቂያ ክምችት እንዲኖር መደረጉን ያረጋግጣል፣

፲፬. ባሕላዊ የማዕድንና ማምረቻ ሥራን ያበረታታል፣ የኮንስትራክሽን ማዕድን የማምረት ሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣

፲፭. የማዕድን ሀብትን በመጠበቅ ረገድ ከማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር ይተባበራል፣በክልሉ ውስጥ ለሚካሄደው የማዕድንና ኢንርጂ ልማት ሥራዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣

፲፮. የአፋር ሕዝብ ካለበት የተበታተነ የዘላንነት ኑሮ እንዲላቀቅ፣ ዘለቄታ ያለው የተረጋጋ ቋሚ ኒሮ ለመመሥራት በሚካሄደው ቀጣይ ሥራ ልዩ ትኩረት በመስጠት የበኩሉን ሥራ ያከናውናል።

<u>አንቀጽ ፭</u>

<u>የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የትምህርትና ባህል ቢሮ ስልጣንና ተግባር</u>

<u>የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የትምህርትና ባህል ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፣</u>

፩. በሀገሪቱ የትምህርት ፖሊስ መሰረት የክልሉን የትምህርት እቅድና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

፪. በክልሉ ባህል፣ ኪነጥበብ፣ ሥነ ጥበብና የፈጠራ ችሎታ እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያደርጋል፣

፫. በክልሉ ለትምህርት የደረሱ ሁሉ የመማር እድል የሚያገኙበትን ስልት ይቀይሣል፣ መሰረት ትምህርት ለሁሉም እንዲደርስ ያደርጋል።

፱. የማስታወቂያና ባህል ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያ ተከትሎ በክልሉ የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶች ተፈላገው እንዲገኙ፣ እንዲጠበቁ፣እንዲጠገኑ፣እዲታደሱና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ ቅርሶችንና በመጥፋት ላይ ያሉ ባህሎችን ከዝርዝር መግለጫ ጋር ይመዘግባል፣

ክፍል ፰ የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር ፮ ሐምሌ ፭ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

፭. የክልሉ የትምህርት ጥራት በሀገር አቀፍ የተወሰነለትን ስታንዳርድ የተበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፮. የሀገሪቱን የትምህርት ፖሊስና ስታንዳርድ ተከትሎና የክልሉ የአካባቢ ሁኔታዎችን በማገናዘብ የክልሉን የአንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሥርዓት ትምህርት ያዘጋጃክ፣በሥራ ላይ ያውላል፣

፯. በየደረጃው ለማስተማር ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎችን ያስለጥናነል፣ እንዲሰለጥኑም ያደርጋል፣

፰. በሀገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅተው ለክልሉ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ፈተናዎች ተከታትሎ ያስፈጽማል፣ በክልሉ ደረጃ ተዘጋጅተው የሚሰጡትን ፈተናዎችና የምስክር ወረቀቶች ብቃት ያረጋግጣል፣

፱. በክልሉ ውስጥ በማንኛውም ሰው፣ማኅበር ወይም የሃይማኖት ድርጅት ወይም ተቋም እጅ የሚገኙ ቅርሶች በሚገባ እንዲያዙ ድጋፍ ይሰጣል፣

፲. ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑ መጻሕፍትና ሌሎች የትምህርት መሣሪያዎች እንዲሟሉ ያደርጋል።

፲፩. በክልሉ ውስት የሕዝብ ቤተጻሕፍት፣ ቤተመዛግብትና አብያተ መዘክሮች/ሙዚየሞች/እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ ያደርጋል፣

፲፪. የክልሉን የአንደኛና የሆለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና ለወደፊት በክልል መንግሥት የሚቋቋሙትን መለስተኛ ኮሌጆች ያደራጃል፣ ያስተዳድራል።

፲፫. በሀገር ውስጥ ድርጅቶችና ባለሀብቶች ለሚቋቋሙ እስከ 2 ኛ ደረጃ ለሚሆኔ ት/ቤቶች ፈቃድ ይሰጣል፣ የብቃት ደረጃውን ለማረጋገጥ፣ ይቆጣጠራል፣

፲፬. በክል ፊልምቤቶች፣ ቴያትር ቤቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣

፲፭. ለሴቶች፣ለሕጻናትና ለጎልማሶች ለሚሰጡ የትምህርት አገልግሎቶች ልዩ ድጋፍ ይሰጣል።

፲፮. ለትምህርት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚሆኑ ፕሮጀክቶች ያዘጋጃል፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

፲፯. የክልሉ የትምህርት ፕሮግራም በመገናኛ ዘዴዎች እንዲደገፉ ያደርጋል፣

፲፰. ለትምህርት ሥራ ለማሻሻል የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄድ ጥናቶች አስፈላጊውን ድፋፍ ይሰጣል።

፲፱. የክልሉ ታሪክና ባህል ተመዝግቦ እንዲያዝ ቋንቋዎች እንዲጠኑና ሥነ ጽሁፎቻቸው እንዲዳብሩና እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ በት/ቤቶችም ውስጥ በአፋርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመዛዛል፣ያስፋፉል፣

፳፩. በክልሉ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ልዩ ልዩ የተማሪዎች አገልግሎቶችን ያስተላልፋል፣

፳፪. ለትምህርት ሥራ አስፈላጊ የሆነው ድጋፍ ለማግኘት እንዲቻል ሕብረተሰቡን ያስተባብራል።

፳፫. የአፋር ሕዝብ ካለበት የተበታተነ የዘላንነት ኑሮ እንዲላቀቅ ዘለቄታ ያለው የተረጋጋ ቋሚ ኒሮ ለመመሥረት በሚካሄደው ቀጣይ ሥራ ላዩ ትኩረት በመስጠት የበኩሉን ሥራ ያከናውናል።

<u>አንቀጽ ፮</u>

<u>የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጤና ቢሮ ሥልጣንና ተግባር፣</u>

<u>የጤና ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣</u>

፩. የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲ መሰረት በማድረግ የክልሉን ሕዝብ ጤና የሚጠበቅበትን ዕቅድና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

<u>ገጽ፮ የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር ፮ ሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም</u>

፪. ስለሕዝብ ጤና ጥበቃ የወጡ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፣ የማዕከላዊውን መንግሥት ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ የአፈጻጸም መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ያውላል።

፫. በክልሉ መንግሥት ውስጥ የሚቋቋሙትን ሆስፒታሎችን፣ጤና ጣቢያዎች፣ ክሊኒኮችን፣ የምርምር የማሰልጠኛ ተቋማትን ያደራጃል ያስተዳድራል፣

፬. በሀገር ውስጥ ድርጅቶችና ባለሀብቶች ለማቋቋሙ ጤና ጣቢያዎች፣ ክሊኒኮች ላቦራቶሪዎችና ፋርማሲዎች ፈቃድ ይሰጣል፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጣውን ደረጃ ጠብቀው መሥራታቸውን ይቆጣጠራል።

፭. ፍቱንነታቸው የተረጋገጠ የባህል መድኃኒሮች የሕክምና ዘዴዎች ከዘመናዊ ሕክምና ጋረ ተዋሕደው ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

፮. በክልሉ ውስጥ በሕዝብ ጤና አገልግሎት ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች የተወሰነ ደረጃ ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፣

፯. ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለማጥፋት ክትባቶች እንዲሰጡና ሌሎች ተገቢ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፣

፰. የሕዝቡን ለጤና ለመጠበቅ በሚደረግ የኳራንቴን ቁጥጥር ይሣተፋል፣

፱. የምግቦች ለጤና ተስማሚነት ያረጋግጣል፣

፲. ስለ ሥራው አፈጻጸም ወቅታዊ ዘገባዎችን እያዘጋጀ ለክልሉ ም/ቤትና ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ያቀርባል፣

አንቀጽ ፯

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ንግድ፣ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርትና ቱሪዝም ቢሮ ሥልጣንና ተግባር፣

የንግድ ኢንዱስትሪ፣ትራንስፖርትና ቱሪዝም ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

፩. የሀገሪቱን የንግድ፣ የቱሪዝም፣ የኢንዱስትሪና ዕደጥበባት እና የትራንስፖርትና መገናኛ ፖሊሲ መሰረት በማድረግ በክልል ውስጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣የትራንስፖርትና መገናኛ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ የኢንዱስትሪና ዕደጥበባት ልማት እንዲጎለብት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

፪. የንግድ እንቅስቃሴዎችን የቱሪዝም የትራንስፖርትና መገናኛ አገልግሎቶችን ለመቆጣጠር የወጡ ሕጎች፣ ደንቦች መመሪያዎች በክልሉ መከበራቸውን ያረጋግጣል።

፫. ለሌሎች አግባብ ላላቸው አካላት የተሰጠውን ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል መንግሥትን የትራንስፖርትና መገናኛ አገልግሎቶች እንዲሰሩ እንዲሻሻሉና እንዲጠገኑ ያደርጋል፣

፬. በክልሉ መንግሥት ወስጥ በሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ለሚካሄዱ የንግዱ ሥራዎች የኢንዱስርሪ ዕደ ጥበባት በሕዝብ መንገድ ማመላለሻና ሰዎችና ድርጅቶች ፈቃድ ይሰጣል፣ የተወሰነላቸው ደረጃ መጠበቃቸውን ይቆጣጠራል፣

፭. ይሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ማህበሮችን ይመዘግባል፣ በማህበራቱ የሚቀርቡለትን የስምሪት ፕሮግራም ያጸድቃል፣ ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራል፣

<u>ገጽ፯ የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር ፭ ሐምሌ ፭ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም</u>

፮. በክልል መንግሥት ውስጥ የሚገኙ ተሸከርካሪዎችን ይመዘግባል፣ በነዚሁ ላይ የቴክኒክ ምርመራ ያደርጋል፣ የመንጃ ፈቃድ ይሰጣል፣

፯. በክል መንግሥት ውስጥ የትራንስፖርትና የመገናኛ ዓይነቶች ተደጋግፈው የሚያድጉበትንና በተቀነባበረ ሁኔታና በሚገባ በጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

፰. በክልሉ መንግሥት ውስጥ የመሰረታዊ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ሥርጭትን አግባብ ባለው አካል የተወሰነው የዋጋ ተመን መከበሩን ይቆጣጠራል፣

፱. የክልል መንግሥት የኢንዱስትሪ፣ የእርሻና ሌሎች ውጤቶች እንዲታወቁ ኤግዚቪሽን እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣

፲፩. የኢንዱስትሪ፣ ፕሮጀክቶች ሃሳቦችና እያመነጨ በማዕከላዊ መንግሥት ሲጠኑና ሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባቸውን ለንግሥት ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ያስተላልፋል፣ ሌሎችም በክልሉ ደረጃ እንዲጠኑና በሥራ ላይ እንዲውሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

፲፪. ለዕደ ጥባባት፣ ለጎጆ እንዱስትሪዎች ለአነስተኛ ኢንዱስትራዎች የኤክስቴንሽን አገልግሎት ይሰጣል፣ እንደአስፈላጊነቱ የዕደ ጥበባትን የጎጆ ኢንዱስትሪዎች የሙያ ማሻሻያ ማሰልጠኛ ማዕከላትን፣ የሕዝብ የንግድ፣ የመንገድ ማመላለሻ ተሸከርካሪዎች መናኸሪዎች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፣

፲፫. በክልል መንግሥት ውስጥ ለሚቋቋመው መካከለኛና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች የተሸከርካሪ መጠገኛ ማደሻጋራጆችና ባለሞተሮች ተሸከርካሪዎች መንዳት ለሚያስተምሩ ሰዎችና ድርጁቶች ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች የሕብረት ሥራ ማኅበራት ይመግባል፣

፲፬. በክልሉ የሚቋቋሙ የንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤቶችን ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል።

፲፭. የንግድ የቱሪዝም፣የትራንስፖርትና መገናኛ የኢንሱስትሪና ዕደ ጥበባት ልማት የሚመለከሩ መረጃዎች ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል።

፲፮. የክልሉ የንግድ መዝገብ ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፣

አንቀጽ ፮

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአደጋ መከላከልና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር፣

የአደጋ መከላከልና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

፩. የሀገሪቱን የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ፖሊሲዎች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

፪. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር አደጋን ለመከላከል የተቀየሱ ፖሊሲዎችና ስልቶች በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

፫. አሰሪና ሰራተኛን በሚመለከት የወጡ ሕጎች፣ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፣

፬. የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የወጡ የሥራ ሁኔታ ደረጃዎችና የመከላከያ ዘዴዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፣

፭. በክልሉ አጋ በተከሰተ ጊዜ የደረሰውን ጉዳትና መወሰድ የሚገባውን እርምጃ ለዚሁ የሚያስፈልገውን ድጋፍ በዝርዝር የሚያመለክት ዕቅድ ያዘጋጃል፣

፮. የእርዳታ ግኝትና አስተዳደርን በሚመለከት የማዕከላዊ መንግሥት በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ከዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፣

፯. በክልሉ የሚቋቋሙትን የሰራተኛና የአሰሪ ማህበራትን ይመዘግባል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣

፰.በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ለክልሉ የተደለደለውን እርዳታ ለተረጂዎች መዳረሱን ያረጋግጣል፣

፱. የሕብረት ስምምነት ድርጅቶችና የሥራ ክርክሮች በሕግ የተዘረጋውን ሥርዓት ተከትለው ፈጻሜ እንዲያገኙ በተቀላጠፈ ሁኔታ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል የሕብረት ስምምቶችን ይመዘግባል፣

፲. ለዕርዳታ ፕሮግራሞች የማስፈፀሚያ የሚያስፈልጉ ልማት ነክፕሮጀክቶችን ዝግጅትና አፈጻጸም ያስተባብራል።

፲፩ ለክልሉ ስለተሰማራው የሰው ኃይልና ስል ሙያ አመዳደብ ጥናት ያደርጋል፣

፲፪. በክልሉ ውስጥ ሥራ ፈላጊዎች ክፍት የሥራ መደቦች እንዲመዘገቡና ሥራና ሰራተኛን እንዲያገናኙ ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

፲፫. በክልሉ እንዲሰሩ በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የሚመደቡትን መንግሥታዊ ያልሆኑ ዕርዳታ ሰጪ ድርጁቶች ሥራ ያስተባባራል፣ ስለሥራቸው አፈጻጸምና ብቃታቸውንም ለኮሚሽኑ ሪፖርት ያደርጋል፣

፲፬. ስለ ክልሉ የሰው ኃይልና የሥራ ስምሪት ስለሰራተኞች ደህንነትና ጤና እንዲሁም አሰሪና ሰራተኛን በሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል።

፲፭. በዘለቄታ ጡረታና የማህበራዊ ዋስትና ዕቅድ የሚሸፈኑ የክልሉ ሰራተኞች በመብታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል፣

፲፮. ሴቶች በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣በማህበራዊና በባህል መስኮች ያላቸውን ተሳትፎ ለማጎልበት የወጡ ፖሊሲዎች በክልሉ ሕብረተሰብ ተግባር ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

፲፯. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ሕጻናትና ወጣቶች መልካም አስተዳደግ እንዲያገኙ ለማድረግ ዘዴዎች በክልሉ እንዲዘረጉ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል።

፲፰. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የሚገኙ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል።

፲፱. የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች እንዲወገዱ የክልሉን ሕብረተሰብ ያስተባብራል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣

፰. የቤተሰብ ደህንነት እንዲጠበቁ ለማድረግ የጋብቻ ሥርዓትን ለመንከባከብ የሚወጡ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ያደርጋል።

አንቀጽ ፱.

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

፩. የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች አስተዳደርን በሚመለከት የሰው ኃይል ፖሊሲዎችን በሚመለከት በሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል።

፪. የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ያወጣውን የሥራ መደቦች አመዳደብ መመሪያ ተከትሎ በክልል መንግስት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የሥራ መደቦች ይመድባል፣

፫. ለመንግሥት ሰራተኞች የተፈቀደው የደመወዝ እስኬል፣ የልዩ ልዩ አበሎች ክፍያና ሌሎች የሥራ ሁኔታዎች የክልል መንግስትን የመንግሥት ሰራተኞች በሚመለከት በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

፬. የክልል መስተዳድሩ የመንግስት ሰራተኞች አቀጣጠር፣ አመዳደብ ደረጃ ዕድገትና የደመወዝ ጭማሪ፣ ዝውውር፣ ሥልጣናንና የዲሲፕሊን አጠባበቅ በመንግሥት ሰራተኞች ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት እንዲፈጸም ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል።

፭. የክልል መንግሥትን የመንግስት ሰራተኞች ዝርዝር ሁኔታ መዝግቦ ይይዛል ስታትስቲካዊ መረጃዎችን ኪሚሽንም ያስተላልፋል።

፮. የክልል መንግሥትን የመንግሥት ሰራተኞች ከጡረታ ዕድሜ ክልል በላይ አገልግሎታቸው እንዲራዘም በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል፣

፯. የክልል መንግስቱ የመንግስቱ ሰራተኞች ችሎታ ማነስ ምክንያት ከሥራ ለማሰናበት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል፣

፰. የክልል መንግስቱ የመንግስት ሰራተኞች ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በሚያቀርቡት ይግባኝ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል፣

፱. ለመንግስት ሰራተኞች የሥራ ውጤት መመዘኛ የወጣው መመሪያ በአስተዳደር መ/ቤቶች ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፣

፲. የክልሉ መ/ቤቶች የጊዜያዊ ሰራተኞችን ቅጥር በተመለከተ የወጣውን መመሪያ ተከትለው መፈጸማቸውን ይቆጣጠራል፣

፲፩. የመንግስት ሰራተኞች ፌዴራል ሕጉችን፣ ዶክመንቶችንና መመሪያዎችን በመተርጎም ረገድ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ያስተልልፋል፣

፲፪. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የመስተዳድሩን መ/ቤቶች አደረጃጀትና የሰው ኃይል አጠቃቀም በመገምገም የማሻሻያ ሀሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራና ሰራተኛ መገናኙቱን ያረጋግጣል።

አንቀጽ ፲

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኦዲት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር፣

ኦዲት ቢሮ ተጠሪነቱ ለክልሉ ም/ቤት ሆኖ ኃላፊነትን ለመወጣት እንዲችል ሥልጣንና ተግባሩ እንደሚከተለው ይሆናል።

፩. የክልሉ ም/ቤት ጽ/ቤትንና በክልሉ ኃላፊነት ሥር የሚገኙ መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን እንዲሁም ማህበራትን ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል።

፪. ያከናወነውን ምርመራ ውጤት እንደሁኔታው ለሚመለከተው መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ያሣውቃል።

፫. አንድ ሂሣብ ተንኮል በተሞላበትና ታማኝነት በጎደለው ሁኔታ መያዙን ለማመን ምክንያት ሲኖሮው ይህን ሂሣብ የሚመለከቱ የሂሣብ መዛግብት ሰነዶች መዘክሮችና ሌሎች መሰል መረጃዎችን ያሸጋል።

፬. በክልሉ ውስጥ በግል የሚሠሩ ኦዲተሮችንና ሂሣብ አዋቂዎች በሥራው መስክ ለመስማራት መቻላቸውን የሚያረጋግጣ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፣

፭. የተካሔዱ ምርመራዎችን ይዘት በመርመርመር የችግሮችን መንሰኤ/ምንጭ/ያጠናል፣የመፍትሔ ሃሳብ ያቀርባል።

፮. የሂሳብ የንብረት ኦዲት ሥርዓትና ደረጃን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ያወጣል፣

፯. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አስፈላጊ መስሎ ሲያገኘው ለውስጥ ኦዲትር ሥልጠና ይሰጣል።

፰. የፋይናንስ ቢሮ ስለገንዘብና የሂሣብ አጠቃቀም በሚያዘጋጀው ደንብ ላይ አስተያየትና የሂሣብ ሙያ እንዲዳብር አስፈላጊውን ምክር ይሰጣል።

<u>ገጽ ፲፩ የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር ፯ ሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም</u>

፱. ስለአከናወነው ምርመራና ስለግኝቶች አጠቃላይ ሪፖርት ለክልሉ ም/ቤትና ለዋናዉ ኦዲት መ/ቤት ያቀርባል፣

አንቀጽ ፲፩

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የዉሀ ሃብት ልማት ቢሮ ሥልጣንና ተግባር

፩. የክልሉን አጠቃይ የልማት እቅድ መሰረት በማድረግ የውሃ ልማት እቅድ ያዘጋጃል፣

፪. በክልሉ የውሃ ሀብት ጥናትና ዲዛይን ያከናውናል፣

፫. በክልሉ የሚካሔዱ የውሃ ሃብት ፕሮጀክቶችን ያስፈጽማል፣

፬. የገጠሩ ኅብረተሰብ በውሃ ሀብት ልማት ሥራ ላይ እንዲሣተፍ ያደራጃል፣ ያስተምራል፣ ለኅብረተሰቡ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣

፭. የመጠጥ ውሃ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ያካሂዳል፣

፮. መስኖ ልማት ሥራዎች ያካሒዳል፣

፯. በክልሉ የውሃ ሀብትን የተመለከቱ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣

፰. የከተማ ውሃ አገልግሎትን የኦፕሬሽን አፈጻጸም እየገመገመ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣የውሃ አጠቃቀም ይወሰናል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል።

<u>አንቀጽ ፲፪</u>

<u>የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፍትህ ቢሮ ስልጣንና ተግባር፣</u>

የፍትህ ቢሮ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩. የሕግ ጉዳዮችን በሚመለከት የክልሉ መንግሥት ዋና አማካሪ ሆኖ ይሰራል፣

፪. የክል ፖሊስ ኃይል የክልሉ የማረሚያ ቤት አስተዳደርን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

፫. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በማዕከላዊ መንግስት የወጣው ሕጎች በክልሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ እንዲተረጎም ያደርጋል፣ለወንጀል መከላከል የሚረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል።

፬. በክልሉ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ሥር የሚወድቁ ወንጀሎች የክልሉን መንግሥት በመወከል ይከራከራል፣

፭. የሕዝቡን እንዲሁም የክልል መንግሥትን መብትና ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ በማዕከላዊና በክልል መንግሥት ፍርድ ቤቶች በማንኛውም ዳኝነት ሰሚ አካል ወይም የሽምግልና ጉባኤ ክስ ይመሰረታል፣ ክስ እንዲመሰረት ያደርጋል፣ወይም ጣልቃ በመግባት ይከራከራል፣ እንደነገሩ ሁኔታም ተከላካይ በመሆኑ ይቀርባል፣

፮. የወንጀል ምርመራ ክፍሎች ሥራቸውን በሕግ መሰረት ማከናወናቸውን ያረጋግጣል፣ ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ እንዲደረግ ያዛል፣ በቂ ምክንያት ሲኖር የተጀመረ ምርመራ እንዲቆም ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲቆም ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወን ያደርጋል ወይም ራሱ ይመረምራል፣

፮. የወንጀል መነሻዎችን የመከላከያ ዘዴዎችን ያጠናል፣ ወንጀል የሚቀንስበትን ስልት ይቀይሣል፣

፯. የወንጀል ድርጊት ምስክሮች እንደአስፈላጊነቱ ተገቢውን የሕግ ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፣

፱. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለክልሉ አቃቢያንና ፖሊስ የስልጠና ፕሮግራም ያዘጋጃል።

፲. በክል መንግሥትና የአሰፈጻሚ አካላት ጥያቄ ሲቀርብለት የሕግ ረቂቆች በማዘጋጀት ይረዳል፣

፲፩. እስከ ክልሉ የበላይ ፍርድ ቤት ድረስ መከራከር ለሚችሉ ጠበቆች ፈቃድ ይሰጣል ይቆጣጠራል፣

፲፪. የክልሉን ሕብረተሰብ ንቃት ሕግ ለማዳበር በተለያዩ ዘዴዎች የሕግ ትም/ይሰጣል፣

፲፫. የውልና ምዝገባ ማስረጃ ምዝገባ ጽሕፈት ቤቶች እንዲደራጁ ያደርጋል፣ሥራቸውንም በበላይነት ይመራል፣

ገጽ ፲፪. የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር ፮ ሀምሌ ፭ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

፲፬. ከዲፈክሽንና ሕጎችን የማጠቃለል ሥራ ያካሂዳል፣ የክልሉን ሕጎች ያሰባስባል፣ እንደአስፈላጊነቱም እንዲጠቃለሉ ይደርጋል፣

አንቀጽ ፲፫

የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የአካል ማስልጠኛና ስፖርት ኮሚሽን ስልጣንና ተግባር

የክልሉ የአካል ማስልጠኛና ስፖርት ኮሚሽን የሚከተለው ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

፩. የአገሪቱን የስፖርት ፖሊሲ መሰረት በማድረግ አካል ማሰልጠኛና ስፖርት በክልሉ ውስጥ ያስፋፋል፣

፪. በክልሉ ውስጥ ለሚቋቋመው የስፖርት ማኅበሮች ፈቃድ ይሰጣል፣ፕሮግራማቸውን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

፫. ክልለ አቀፍ ስፖርት ውድድሮችን ያዘጋጃል፣

፬. ክልል አቀፍ የስፖርት ውድድሮችን በሚመለከት በስፖርት ማኅበሮች መካከል የሚነሳውን ክርክር ይዳኛል፣

፭. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ትጥቅም መሣሪያ ከአገር ውስጥ ውይም ከውጭ የሚገባበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

፮. የክልሉ ባሕላዊ ስፖርቶች የበለጠ እንዲታወቁ፣ እንዲሻሻሉና እንዲያድጉ ያደርጋል።

፮. የክልሉ የስፖርት ማኅበሮች ገቢ ለዓላማቸው ብቻ መዋሉን ለማረጋገጥ ሂሳባቸውን ይመረምራል፣

፱. በክልሉና አገር አቀፍ ደረጃ የሚያገለግሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን ያዘጋጃል፣

፲. ከክልሉ ጤና ቢሮ ጋር በመተባበር ስፖርታዊ ሕክምና ያደራጃል፣

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

እስማኤል አለ. ሴሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ርዕስ መስተዳድር